ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ኢየሱስ ክርስቶስ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

The Triumphant Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

---

ቍጥር ፫/፳፻፲ ዓ. ም.

# ቃለ ዐዋዲ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የአዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

**በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤**
**አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤**
**በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥ ወንግሥትነ፡**
**ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤**
**በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥ ወካህንነ፥ ወንጉሥነ**
**ኢየሱስ ክርስቶስ፡**
**ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።**

**+ + +**

# ይድረስ፡-

## ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት
## የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች!

እኛ፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ ከቸሩ ፈጣሪያችን ጋር፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም፡ በሚያገናኘንና በሚያስተሣሥረን፥ በሚያዋሕደንና በሚያኖረን ሃይማኖታችንና ምግባራችን ረገድ፡ ብርቱ ጥንቃቄን ልናደርግበት የሚገባን ጉዳይ፡ በይበልጥ፡ የህልውናችን መሠረት ስለኾነው፡ ስለአምልኳችን ያለን እውቀትና የአፈጻጸሙ ሥርዓት: ትክክለኛ መኾኑን ማረጋገጥ ይኾናል።

ስለዚህ፡ የዚሁ አምልኳችን መገለጫዎች ከኾኑት ርእሶች መካከል፡ እዚህ ላይ፡ በቅድሚያ፡ ስለሰንበትና ስለስግደት፥ ስለድንግል ማርያምና ስለቅዱሱ ኪዳን ተልእኮ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖቷ መሠረት፡ አጽንታ ያኖረችው ምግባራዊ ሥርዓቷ፡ ምን እንደኾነ፡ በግልጽና በትክክል ታውቁት ዘንድ፡ እንደሚከተለው ቀርቦላችኋል።

## ሰንበትን በሚመለከት።

"ሰንበተ አይሁድ" ስለተባለችው፡ ስለቅዳሜ እና "ሰንበተ ክርስቲያን" ስለተባለችው፡ ስለእሑድ፡ ስትሰሙ ኖራችኋል። ይኹን እንጂ፡ "ሰንበት"፡ ጥንትም፥ እስከዛሬና ዛሬም፥ ለዘለዓለምም፡ አንዲት ናት፤ ኹለት ሰንበታት የሉም።

ያች አንዲቷ ሰንበት፡-

በቀዳማዊው የፍጥረት ዘመን፡ "ወባረካ እግዚአብሔር፡ ለዕለት ሳብዕት፤ ወቀደሳ፤ እስመ ባቲ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ፡ ዘአኀዘ ይግበር።"

ማለትም፡ "እግዚአብሔርም፡ ሰባተኛዋን ቀን ባረካት፤ ቀደሳትም፤ የጀመረውን የመፍጠር ሥራውን ኹሉ ፈጽሞ፡ በእርሷ ዐርፎባታልና።" የተባለችው ናት፤

በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡ "ተዘከር፡ ዕለተ ሰንበት፡ ከመ ትቀድሳ! ሰዱሰ ዕለተ ትገብር ኵሎ ግብረከ፥ ወኵሎ ትካዘከ! ወሳብዕት ዕለት፡ ሰንበቱ፡ ለእግዚአብሔር አምላክከ፤ ኢትግበር ባቲ፤ ወኢምንተኒ ግብረ!"

ማለትም፡ "የሰንበትን ቀን ትቀድሳት ዘንድ፡ አስብ! በስድስቱ ቀኖች፡ ሥራህን ኹሉ፥ ግዳጅህንም ኹሉ አድርግ! ሰባተኛዋ ቀን ግን፡ የአምላክህ የእግዚአብሔር ሰንበቱ ናትና፡ በእርሷ፡ አትሥራ! ምንም ዓይነት ተግባርን አታድርግ!" የተባለላት፡ እርሷው ናት፤

በፍጻሜውም የሕይወት ዘመን፡ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ይከውንኑ በሰንበት፡ ገቢረ ሠናይ? ወሚመ፡ ገቢረ እኩይ? አሕይዎ ነፍስኑ? ወሚመ፡ ቀቲል?"

ማለትም፡ "በሰንበት፡ ማድረግ የሚገባው፡ በጎ ነገርን ነውን? ወይስ፡ ክፉ ነገርን? ነፍስ ማዳን? ወይስ፡ መግደል?" ብሎ፡ ለተቃዋሚዎቹ ላቀረበላቸው ጥያቄ፡ መልስ ስላልሰጡት፡ ሕሙማንን በመፈወስ፡ በሰንበት፡ በጎ ማድረግና ማዳን እንደሚገባ፥

ደግሞም፡ "ሰንበትሰ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት፤ ወአኮ ሰብእ፡ በእንተ ሰንበት። ወወልደ እጓለ እመሕያው ውእቱ፡ እግዚኣሃ፡ ለሰንበት።"

ማለትም፡ "ሰንበትማ፡ ስለሰው ተፈጠረች እንጂ፡ ሰው፡ ስለሰንበት አልተፈጠረም። የማርያም ልጅ፡ የሰንበት፡ ጌታዋ ነው።" ብሎ በማብራራት፡ የተናገረላት ናት።

"በአጠቃላዩም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል ላይ ኾኖ፡ "ተፈጸመ ኵሉ!" ማለትም፡ "እንግዴህ፡ ኹሉ አበቃ!" ብሎ፡ ነፍሱን፡ በሥልጣኑ፡ ከሥጋው ከለየ በኋላ፡

"ወአይሁድሰ፡ እስመ ዐርብ ውእቱ፡ ይቤሉ፡ 'እላንቱ ሥጋት፡ ኢይቢታ ዲበ መሳቅሊሆን፡ በእንተ ሰንበት፤ እስመ ዐባይ ዕለታ፡ ለይእቲ ሰንበት!'"

ማለትም፡"አይሁድ ግን፡ መሸቷልና፡ 'እነዚህ አስከሬኖች፡ ስለሰንበት፡ በየተሰቀሉበት አይደሩ! የዚች ሰንበት ቀን፡ ታላቅ ናትና!' አሉ።" የተባለችው፡ ይህችው፡ አንዲቷ ሰንበት ናት። "(ዘፍጥ. ፪፥ ፫። ዘፀአ. ፳፥ ፰-፲፩። ማር. ፪፥ ፳፯-፳፰፤ ፫፥ ፫-፬። ዮሐ. ፲፱፥ ፴፩።)

እንግዴህ፡ ያች፡ "እግዚኣሃ፡ ለሰንበት" ማለትም፡ "የሰንበት፡ ፈጣሪዋና ጌታዋ የኾነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነቱ ሞቶ ሣለ፡ መለኮትን የተዋሓደ ሥጋውን፡ በመቃብር አሳድሮ ያረፈባት፥ ነጻነትንም ለማወጅ፡ በነፍሱ፡ ወደሲዖል ወርዶ ያሳለፋት፡ የሰሙነ ሕማማቷ ሰንበት፡ ይህችው አንዲቷ ሰንበት ናት።

በሥጋዊው የፍጥረት ባሕርይና ሥርዓት፡ በአንዲት ቀን ተወስና፡ በሰዎች ሥርዓትና ይትበሃል፡ "ቅዳሜ"፥ "ቀዳሚት ሰንበት"፥ "ሰንበተ አይሁድ" እየተባለች የቆየችው፥ በመጨረሻ ግን፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ ወሰን የሌላት ሕያውትና ዘለዓለማዊት ለመኾን የበቃችው፡ ይህችው፡ አንዲቷ ሰንበት ናት።

"ሰንበተ ክርስቲያን" የተባለችው፡ ሌላ፥ ወይም፡ ኹለተኛ ሰንበት አይደለችም፤ ይህችው፡ በዘልማድ፡ "ቅዳሜ"፥ "ቀዳሚት ሰንበት"፥ "ሰንበተ አይሁድ" እየተባለች የኖረችው፥ ከፍጥረት ልደት ጀምሮ፡ "ሰንበተ ኢትዮጵያ" ኾና፡ በህልውናዋ የቀጠለችው፡ አንዲቷ ሰንበት ናት እንጂ።

አዎን! ከዚህ የተነሣ፡ ከመጨረሻው፡ የትንሣኤ ዘጉባኤ በፊት፡ "ብፁዕ ወቅዱስ ውእቱ፡ ዘረከበ ክፍለ፡ በትንሣኤ እንተ ትቀድም መጺአ!"

ማለትም፡ "አስቀድማ በምትመጣው ትንሣኤ፡ ዕድል ፈንታ ያገኘ ሰው፡ ብፁዕና ቅዱስ ነው!" ተብሎ እንደተነገረው፡ ዛሬም እንኳ፡ በዚሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በተገኘው፡ በመጀመሪያው፡ የሺሁ ዓመት የመንፈስና የትንሣኤ ሕይወት ለመኖር የበቁት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ጭምር፡ ወሰን በሌላት፥ ሕያውትና ዘለዓለማዊት በኾነችው፡ በዚችው፡ በአንዲቷ ሰንበት፡ እነሆ ይኖራሉ። (ራእ. ፳፥ ፮።)

ሌላ ኹለተኛ ሰንበት ያለች ይመስል፡ ይህችው፡ አንዲቷ ሰንበት፡ "ቀዳሚት" ወይም፡ "ቅዳሜ" የሚል መለያ ስም ተሰጥቷት መኖሯ፥ ደግሞም፡ "ሰንበተ አይሁድ" ማለትም፡ "የአይሁድ ሰንበት" እየተባለች መጠራቷ፥ ይልቁንም፡ "ቅዳሜ ስዑር"፥ ወይም፡ "ከሰንበትነቷ የተሻረች ቅዳሜ" ስትባል መኖሯ፡ አግባብ እንዳልኾነ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የተከሠተችው፡ የእግዚአብሔር እውነት አረጋግጣ አመልክታለች። የሰንበት ጌታ እርሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሥጋው ሞቶ፡ በመቃብር ዕረፍቱ፡ ያሳለፋት ስለኾነች፡ ዕለቷ፡ ከሰንበትነቷ እንደተሻረች በመቍጠር፡ ይህ፡ ልዩ ስያሜ ተሰጥቷት መቆየቱ፡ ፍጹም ስሕተት መኾኑ፡ "በእውነትና በመንፈስ" አምልኮ ጸንታ በምትኖረው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ እሙን ነው።

"ቅዳሜ ስዑር" በተባለችው፡ በዚችው ዕለት፡ የኾነውን መለኮታዊ ድርጊት፡ በእውነት አስተውለው ሲመለከቱት፡ ጌታ፡ በመቃብር ውስጥ፡ በሥጋው ያረፈባት በመኾኗ፡ በአንድ በኩል፡ "**ተዘከር፡ ዕለተ ሰንበት፡ ከመ ትቀድሳ!**" ማለትም፡ "**የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ!**" በምትለው፡በዓሠርቱ ቃላት መሠረት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዕለቲቱን፡ በሰንበትነቷ አከበራት እንጂ፡ አልሻራትም፤ በሌላው በኩል ደግሞ፡ በትንሣኤው፡ ይህችኑ አንዷቷን ሰንበት፡ ሕያውትና ዘለዓለማዊት ኾና እንድትቀጥል አድርጓታል።

በዚህ መሠረት፡ ይህችው፡ አንዲቷ ሰንበት፡ በአንድነቷ ጸንታ፡ በሕያውነትና በዘለዓለማዊነት ቀጠለች እንጂ፡ "ሰንበተ ክርስቲያን" የተባለች፡ ሌላ ኹለተኛ ሰንበትን አላስገኘችም። ጥንቱንም፡ ይህችኑ፡ አንዲቷን ሰንበት የፈጠረውና ኋላም፡ "**እግዚኡሃ ለሰንበት**" ማለትም፡ "**የሰንበት ጌታዋ**" የተባለው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህችኑ፡ አንዲቷን ሰንበቱን፡ በትንሣኤው፡ ሕያውትና ዘለዓለማዊት አደረጋት እንጂ፡ ሌላ፡ ኹለተኛ ሰንበትን አልፈጠረም፤ አልሠራም። ይህ፡ ኹለት ሰንበታት እንዳሉ የሚያስመስለው ትምህርትና ሥርዓት፡ የሰዎች እንጂ፡ የእግዚአብሔር አለመኾኑ፡ በዚህ እውነታ፡ ተረጋግጦ ይታወቃል።

እስካኹንም ቢኾን፡ "ቅዳሜ ስዑር" መባል ብቻ ሳይኾን፡ "ቀዳሚቷና የብሉይ ኪዳኗ (አሮጌዋ)፥ እንዲሁም፡ የ"አይሁድ" ስትባል የኖረችው፡ ይህችው አንዲቷ ሰንበት፡ "በአዲሱ ኪዳን፡ የጌታ ትንሣኤ ታድሳ፡ በሕያውትነቷና በዘለዓለማዊትነቷ መቀጠሏን ለማሳየትና ለማረጋገጥ፡ 'ሰንበተ ክርስቲያን' ተባለች!" ቢባል፡ አስታራቂ አሳብ ኾኖ፡ ኹሉንም ሊያስማማ ይችላል።

ስለዚህ፡ ይህ፡ የሰንበትን ምንነት የሚገልጠው፡ ታላቅ መለኮታዊ ምሥጢር የተፈጸመውና የተከሠተው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የመስቀል መከራና ሞት፥ መቃብርና ትንሣኤ በመኾኑ፡ ይህችው፡ አንዲቷ ሰንበት፡ እንዲህ፡ "ቅዳሜ" እና "እሑድ" በተባሉት ቀናት፡ "ቀዳሚት ሰንበት" እና "ሰንበተ ክርስቲያን" ተብላ እየተጠራች ስትከበር የኖረችበትን ምክንያት፡ ከላይ በተገለጸው፡ የምሥራቹ ዝክረ ነገር፡ አስፋፍቶ ማስረዳት፡ አዳጋች አይኾንም። ብፁዕ መነኰስ ኤዎስጣቴዎስን የመሰሉት ደጋጎቹና እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሲጋደሉላት የኖሩት የእግዚአብሔር እውነት፡ ይህችው ቍም ነገር ናትና።

ምሥጢራዊ ዜናዋ፡ እንዲህ፡ ተካትቶ እየተነገረ፡ የዚችው፡ የአንዲቷ ሰንበት ህልውና፡ "ቀዳሚት ሰንበት" እና "ሰንበተ ክርስቲያን" በሚለው የተለመደ ስሟ፡ በዚሁ፡ መልኩና ይዘቱ ቢቀጥል እንደሚሻልና እንደሚገባ፡ እዚህ ላይ ማሳሰቡ፡ አስፈላጊ ይኾናል።

+

## ስግደትን በሚመለከት።

ስግደት፡ ራሱን የቻለ፡ አንድ ብቸኛ ሥርዓት ነው፤ ሌላ መልክና ይዘት የለውም። እርሱም፡ በቀጥታ፡ ለፈጣሪ እግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ፡ የአምልኮ መግለጫና ማረጋገጫ የኾነ፡ ሃይማኖታዊ ምግባር ነው።

ሥጋውያንና መንፈሳውያን ፍጡራን፡ እርስ በርሳቸው፡ ፍቅራቸውንና ታማኝነታቸውን፥ አክብሮታቸውንና ትሕትናቸውን፥ አገልጋይነታቸውንና ተገዢነታቸውን ለመግለጽ፡ በተለያየ መልክና በፈለጉት ይዘት የሚፈጽሙት ሥርዓት፡ "ሰላምታ" ይባላል። ይህም፡ ከስግደት ጋር፡ ምንም ዓይነት አግባብነት የሌለው መኾኑ መታወቅ ይኖርበታል።

ይህን መሠረታዊ ልዩነት፡ ከዚህ ቀጥሎ እንደሚታተተው፡ በሃይማኖታዊ ጥንቃቄና በምግባራዊ ገሃድነት፡ ግልጽ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ይኾናል።

በእውነተኛውና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው ምክንያት፡ ጥንት፡ ከፍጥረት አንሥቶ፡ የኢትዮጵያን ልጆች፡ የወደደና የመረጠ አምላክ፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ የእስራኤልን ልጆች፡ ለእርሱ ስለሚያቀርቡት አምልኳቸው፡ **"ኢትስግድ ሎሙ! ወኢታምልኮሙ! እስመ አነ እግዚእ እግዚአብሔር አምላክከ፡ አምላክ ቀናኢ!"**

ማለትም፡ **"እኔ፡ የኹሉ ጌታ እግዚአብሔር፡ ለአምላክነቴ የምቀና ፈጣሪህ ነኝና፡ 'አማልክት ነን!' ለሚሉ፡ አትስገድላቸው! አታምልካቸውም!!"** ብሎ፡ ገና ከመጀመሪያው፡ አስጠንቅቋቸው እንደነበረ ይታወሳል። (ዘጸአ. ፳፥ ፩-፫።)

ኋላም፡ በመጨረሻው፡ የሕይወት ዘመን፡ ሰው ኾኖ በመጣ ጊዜ፡ ይህንኑ፡ የኢትዮጵያን ልጆች፡ የአምልኮትና የስግደት ሥርዓት፡ **"እስመ እግዚአብሔር መንፈስ ውእቱ፤ ወይሰግዱ ሎቱ፡ በመንፈስ፥ ወበጽድቅ፡ ሀለዎሙ ይስግዱ ሎቱ።"**

ማለትም፡ **"እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነው፤ ስለዚህ፡ የሚያመልኩት፡ በመንፈስና በእውነት ይሰግዱለት ዘንድ አላቸው።"** በሚለው መለኮታዊ ቃሉ፡ አጽንቶላቸው እንደነበረ ይታወቃል። (ዮሐ. ፬፥ ፳፬።)

እንግዴህ፡ በዚህ፡ በማይሻረውና በማይለወጠው፡ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ልጅነታቸውና ዜግነታቸው፥ ካህንነታቸውና ነጋሢነታቸው፡ የአምልኮተ እግዚአብሔር ስግደታቸውን፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ የሚፈጽሙት፡ እያንዳንዳቸው፡ በተዋሕዶ ምሥጢር፡ አንድ ለኾኑት፡ ለሦስቱ መለኮታውያን ባሕርያትና አካላት ብቻ ነው፤ እነዚህም፦

፩ኛ፡ ለቅድስት ሥላሴ፡ ማለትም፡ አንድ አምላክ ለኾነው፡ ለእግዚአብሔር አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው፤

፪ኛ፡ **"ዘእግዚአብሔር አስተጻመረ፣ ሰው፡ ኢይፍልጥ!"** ማለትም፡ **"እግዚአብሔር፡ አንድ ያደረገውን፣ ሰው አይለየው!"** በሚለው የፈጣሪ ቃል፡ ከእግዚአብሔር አብ ጋር፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ አንድ ኾና፡ አንድ ልጁን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በሰውነት ለወለደችለት፡ ለአምላክ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ነው፤ (ማቴ. ፲፱፥ ፮።)

፫ኛ፡ በፍጹም መለኮትነቱ፡ "ወልደ አብ"፡ ማለትም፡ "የአብ ልጅ"፥ በፍጹም ሰውነቱም፡ "ወልደ ማርያም"፡ ማለትም፡ "የማርያም ልጅ" የኾነውና የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ተሰቅሎበት፡ ሥጋውን ቆርሶና ደሙን አፍስሶ፡ ፍጥረተ ዓለሙን ላዳነበት፡ ለቅዱስ መስቀል ነው።

እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ አምልኮተ እግዚአብሔርን በሚመለከት፡ በብርቱ የምንጠነቀቀው፡ ያለምክንያት አይደለም። በዚህ መልክ፡ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርበው ስግደት፡ በሚታይና ግዙፍ በኾነው፡ ሥዕላዊ ኾነ ቅርጻዊ አካል ፊት እንደሚፈጸም፡ የጣዖት አምልኮን በሚመስል ይዘት ሳይኾን፡ የማይታይ ረቂቅ በኾነው፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንዲኾን፡ እጅግ ብርቱ ጥንቃቄን ማድረግ እንዳለብን፡ ያለማሰለስ ለሚያሳስበን መለኮታዊ ቃል፡ ቅድሚያን ሰጥተን መከተልና በተግባር ላይ ማዋል የሚገባን መኾኑን ስለተገነዘብን ነው።

በተለይ፡ ስግደትን በሚመለከት፡ ሰዎች፤ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከሚያውጧጧቸው ጥቅሶቹ መካከል፡ ልንከተልና ልንፈጽም የሚገባን ቃል፡ የትኛው ይኹን? ጥንታዊና ቀዳማዊ፥ አማናዊና ኪዳናዊ የኾነውን ኢትዮጵያዊውን? ወይስ፡ ደኃራዊና ሰብአዊ፥ ኦሪታዊና መቅሠፍታዊ የኾነውን፡ እስራኤላዊዉን?

እኛስ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ የኾንነው ልጆቿ፡ በሃይማኖት የተቀበልነውና በምግባር የምንፈጽመው፡ እንዲህ የሚለውን ቃል ነው፡-

እርሱም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ የእርሱ እኩዮች ልጆቹና አገልጋዮቹ፥ ወንድማማችና እኅትማማች ኾነን ከምንቆጠረው፡ ከሰዎችና ከመላእክት ወገኖች መካከል፡ በአንድ በኩል፡ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ፡ **"ወበዊኦ ጴጥሮስ፡ ተቀበሎ ቆርነሌዎስ፤ ወሰገደ ሎቱ፡ ታሕተ እገሪሁ። ወአንሥአ ጴጥሮስ፤ ወይቤሎ፡ 'ተንሥእ! አነሂ ከማከ፡ ሰብእ!"**

*ማለትም፡* **"ጴጥሮስም፡ በገባ ጊዜ፡ ቆርነሌዎስ ተቀበለው፤ ከእግሩ በታችም ወድቆ ሰገደለት። ጴጥሮስም፡ 'ተነሥ! ብሎ፡ በእጁ ቀና አድርጎት፡ 'እኔም እኮ! እንደአንተ፡ ሰው ነኝ!' አለው።"** የሚለው ቃል ሲኾን፤

በሌላ በኩል ደግሞ፡ **"ኢትስግድ ሊተ! ዑቅ! ዮጊ፡ እስመ አነ ገብር ዘከማከ፥ ወዘአኀዊከ ነቢያት፥ ወዘእለ የዐቅቡ፡ ቃለ ዝንቱ መጽሐፍ። አንተሰ፡ ለእግዚአብሔር ስግድ!"**

*ማለትም፡* **"ዕወቅ! ተጠንቀቅ! ለእኔ አትስገድ! እኔም፡ እንዳንተና እንደወንድሞችህ ነቢያት፥ የዚህን መጽሓፍ ቃል እንደሚጠብቁም፡ አገልጋይ ነኝ። አንተስ፡ ለእግዚአብሔር ስገድ!"** ብሎ፡ መልአኩ፡ ለባለራእዩ ዮሓንስ የነገረውን ቃል ነው። እነዚህ ጥቅሶች፡ ለተነሣንበትና ለምንነጋገርበት ርእሰ ነገር፡ ማጠናከሪያ ምስክር ኾነው፡ አማናዊነቱን እንዴት ሊያጸኑት እንደቻሉ፡ ማስተዋሉ አያዳግትም። (የሓዋ. ሥራ ፲፥ ፳፭። ራእ. ፳፪፥ ፱።)

መልአኩ፡ ለዮሓንስ፡ እንዲያ ብሎ፡ አስፋፍቶና አብራርቶ መናገር ያስፈለገው፡ ለዮሓንስ ብቻ ሳይኾን፡ ለእኛና ለእውነተኞች አምላኪዎች ኹሉ ጭምር፡ መመሪያ እንዲኾን ለመኾኑ አያጠራጥርም።

## ድንግል ማርያምን በሚመለከት።

ዲያብሎስና ሠራዊቱ አጋንንት፥ ደግሞም፡ የእነርሱ አገልጋዮች የኾኑ ሰዎች፡ "እግዚአብሔር"፥ ወይም፡ "ኢየሱስ" ከሚለው የስም አጠራር ይልቅ፡ በይበልጥ የሚጠሉትና የሚፈሩት፥ የሚጨነቁትና የሚንቀጠቀጡት፥ የሚታወኩትና የሚራወጡት፡ የድንግል ማርያምን ስም ሲጠሩባቸው እንደኾነ፡ ርኩሳን መናፍስቱ ኹሉ፡ የተቆራኙትን ሰው፡ በውግዘት ለቅቀው እንዲወጡ የሚደረገው፥ እነዚሁ፡ ርኩሳን መናፍስቱ፡ ታሥረው፡ ወደሲዖል እንዲወርዱ የሚበየንባቸውም፡ በድንግል ማርያም ስም እንደኾነ፡ በይፋ ይታወቃል።

እነዚሁ፡ ዲያብሎስና ሠራዊቱ ሰይጣናት፥ ከጭፍሮቻቸው ሰዎች ጭምር፡ ከድንግል ማርያም ስም አጠራር ጋር ዐብረው የሚጠሉትና የሚሸሹት፥ የሚሠቀቁትና አጥብቀው የሚቃወሙት፡ አንድ፡ ተጨማሪ ግሩም ኃይል ደግሞ አለ፤ እርሱም፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት እናቱ በወረሰው ሰውነቱ፡ ፍጥረተ ዓለሙን ያዳነበትን፡ ቅዱስ መስቀሉን ነው።

ዲያብሎስና ርኩሳኑ መናፍስት፥ እንዲሁም፡ ጭፍሮቻቸው ሰዎች፡ የድንግል ማርያም ስም ሲጠራባቸው፡ እንዲህ የሚኾኑት፡ ለምንድር ነው? መልሱ፡ ቀጥታና ግልጽ ነው፤ ያም፡ "እግዚአብሔር ወልድ፡ በመለኮትነቱ፡ በንጽሕትና ቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ተፀንሶና ተወልዶ፡ እነዚህን፡ የክፋት፥ የኃጢኣትና የሞት አበጋዞች፡ እነርሱ፡ ቀፍቅፈው ካመጧቸው፡ የእግዚአብሔር ተፃራሪዎች ከኾኑት ጠንቆቻቸው ጋር፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ለዘለዓለም ደምስሶ ያስወገዳቸው፡ ከእርሷ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በወረሰው፡ በፍጹሙ የነፍስና በፍጹሙ የሥጋ ሰብአዊ አካሉና ባሕርዩ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ የመስቀል ፈተናንና መከራን በመቀበሉ፥ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶና ክቡር ደሙን አፍስሶ፡ በመሥዋዕትነትና በቤዛነት በማቅረቡ፥ በመሞቱና በመቀበሩ፥ በመነሣቱና በማረጉ ነው!" የሚለው ነው።

ይህን፡ በይፋ ተረጋግጦ የታወቀ፡ ገሃድ እውነታ፡ አፅራረ መንፈስ ቅዱስ ሳይቀሩ፡ ሊያስተባብሉትና ሊክዱት የሚሞክሩት አይደለም።

የጌታ የቅርብ ታማኝ የኾነው ደቀ መዝሙሩና ሓዋርያው፥ ወንጌላዊውና ባለራእዩ ዮሓንስ፡ "አኀዊነ! ለኵላ መንፈስ ኢትእመንዋ፤ አላ፡ አመክርዋ ለመንፈስ፣ ለእመ እምኀበ እግዚአብሔር ይእቲ፤ እስመ ብዙኃን ሓሳውያነ ነቢያት መጽኡ ውስተ ዓለም።

"ወበዝንቱ፡ ተአምርዋ ለመንፈሰ እግዚአብሔር፣ ወለመንፈሰ ሓሰት። ኵላ መንፈስ እንተ ታአምን፡ ከመ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መጽአ በሥጋ ሰብእ፡ እምነ እግዚአብሔር ይእቲ። ወኵላ መንፈስ፡ እንተ ኢታአምን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከመ መጽአ በሥጋ ሰብእ፡ ኢኮነት እምነ እግዚአብሔር፤ ወዝንቱ ውእቱ ሓሳዌ መሢሕ፡ ዘሰማዕክሙ ከመ ይመጽእ፤ ወይእዜኒ፡ ወድአ መጽአ፤ ወውስተ ዓለም ሀሎ።"

ማለትም፡ "ወዳጆች ሆይ! መንፈስን ኹሉ አትመኑ፤ ነገር ግን፡ ያ መንፈስ፡ በእውነት የእግዚአብሔር እንደኾነ መርምሩ! ብዙዎች ሓሰተኞች ነቢያት፡ ወደዓለም መጥተዋልና።

"የእግዚአብሔርን መንፈስና የሓሰትን መንፈስ ለይታችሁ የምታውቁበት ምሥጢር ይኸውላችሁ! ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነት እንደመጣ የሚያሳምን መንፈስ፡ ከእግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነት እንደመጣ የማያሳምን መንፈስ ግን፡ ከእግዚአብሔር አይደለም። እንደሚመጣ የሰማችሁትና የክርስቶስ ተቃዋሚው የኾነው፡ ሓሰተኛው መሢሕ፡ እንግዴህ፡ ይህ ሓሰተኛው መንፈስ ነው፤ እርሱም፡ አኹን፡ ፍጽሞ መጥቷል፤ በዓለም ውስጥም አለ።" ብሎ፡ የጻፈውን ቃል፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ አግባብ ይኾናል። (፩ኛ ዮሓ. ፬፥ ፩-፫።)

ይህ ስመ ጥሩ ሓዋርያ፡ "ከመ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽአ በሥጋ ሰብእ" ማለትም፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነት እንደመጣ" ሲል፡ ምን ማለቱ፥ ወይም፡ ማንን ማመልከቱ ነው? እግዚአብሔር ወልድ፡ ከሥጋዋ ሥጋን፥ ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ፡ ፍጹም ሰው የኾነባትን፡ እናቱን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን ማለቱና እርሷን ማመልከቱ አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ነው።

ከሓዲው መንፈስና የሓሰቱ አባት ዲያብሎስ፥ እንዲሁም፡ ሠራዊቱ አጋንንትና ፀረ ማርያሙ ኹሉ፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ለምን እንደሚጠሉና እንደሚቃወሙ፡ ምክንያቱን፡ እንዲህ፡ በቀላሉ ለመገንዘብ፡ ለማንም አስተዋይ ተመልካች የሚያዳግት አይደለም።

ኹሉን ማድረግ የማይሳነው እግዚአብሔር፡ በፈጣሪነት ችሎታው፡ ቀደም ብሎ እንዳሳየው ኹሉ፡ ከድንግል ማርያም ሰው መኾን ሳያስፈልገው፡ በአምላክነቱ ክሂሎት ብቻ፡ ፍጥረተ-ዓለሙን ማዳን እንደሚችል፡ አያጠያይቅም። ታዲያ! ለምን፡ ከእርሷ፡ ከድንግል ማርያም፡ ሰው ለመኾን ፈለገ? የዚህ ምክንያትማ፡ እርሱ፡ በመልኩ ፈጥሮ፡ በእርሱ ክብር እንዲኖር ያዘጋጀውን ሰውን፡ ዲያብሎስ፡ በእባብ አካልና ባሕርይ ተሠውሮ እንዳሳተበት ኹሉ፡ እንዲሁ፡ እርሱ፡ እግዚአብሔርም፡ "እኔ፡ ኹሉን ማድረግ የምችል፡ ፈጣሪ ነኝ!" ሳይል፡ ያንን፡ በራሱ ፍላጎትና ምርጫ፡ ያጠፋውንና የጠፋውን፡ የዚያኑ፡ የፍጡሩን፡ የሰውነት አካልና ባሕርይ ለብሶ፥ ተገቢውንም ካሣ ከፍሎ፡ በእውነተኛና በትክክለኛ ዳኝነቱ፡ ፍጥረቱን ለማዳን ስለፈለገ ነው።

ይህንም እውነታ፡ ገና በፍጥረት መጀመሪያ ላይ፡ እግዚአብሔር፡ "ወኵሎ መዋዕለ ሕይወትከ፡ አስተፃርር ማእክሌከ ወማእከለ ብእሲት፥ ማእከለ ዘርእከ ወማእከለ ዘርኣ፤ ውእቱ፡ ይዕቀብ ርእሰከ፤ ወአንተኒ፡ ዕቀብ ሰኰናሁ።"

ማለትም፡ "በሕይወትህ ዘመን ኹሉ፡ በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋ መካከል፡ ጠላትነትን አጸናለሁ። እርሱ፡ እያደባ፡ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም፡ እያደባህ ሰኰናውን ትነክሣለህ።" ብሎ፡ በእባቡ ዲያብሎስና በሴቲቱ ሔዋን ላይ ያሰሰማው፡ የፍርድ ቃሉ፡ አማናዊ ተፈጻሚነትን ያገኘው፡ በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምና ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ ጋር ባካኼዱትና በእነርሱ ድል አድራጊነት ባበቃው ተጋድሏቸው መኾኑን፡ ማንም አስተዋይና ሃይማኖታዊ ተመልካች ይገነዘበዋል። (ዘፍጥ. ፫፥ ፲፬-፲፭።)

ከዚህ ጋር በተያያዘ፡ የሚቀርብና የሚብራራ፡ ተጨባጭ እውነታ አለ፤ ይኸውም፡ "ቅድስት ድንግል ማርያም ባትኖር ኖሮ እኮ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው ኾኖ፡ ፍጥረተ ዓለሙን፡ በቤዛነቱ ለማዳን ባልቻለ ነበር።" የሚለው ነው። አዎን! ኹሉን ለማድረግ የማይሳነው አምላክ፡ ያለእርሷ፡ ፍጥረተ-ዓለሙን ማዳን ሲቻለው፡ ለምን፡ ከእርሷ፡ በሰውነት መወለድ አስፈለገው? ከእርሷ በፊትም፡ እጅግ ብዙዎች ሴቶች የነበሩ ሲኾን፡ ሰው ኾኖ ለመወለድ፡ ለምን፡ እስከእርሷ ድረስ ጠበቀ? ራሷን፡ ለእግዚአብሔር እናትነት ያበቃች፡ ድንግል ሴት ባለመገኘቷ አይደለምን? አዎን! ነው። አምላክ፡ ፍጥረተ ዓለሙን የሚያድነው፡ ሰው በመኾን ከኾነ፡ ያ ሰውነት፡ ታዲያ ማን ኾነ? የድንግል ማርያም ሰውነት አይደለምን? አዎን! ነው። እንዲህ ከኾነ፡ ፍጥረተ-ዓለሙ የዳነው፡ መለኮት በተዋሓደው በድንግል ማርያም ሰውነት መኾኑ ጥርጥር የሌለበት፡ የሃይማኖታችን መሠረት ነው።

ዳግመኛም፡ "ቃል፡ ሥጋ ኮነ!" ማለትም፡ "ቃል ሥጋ ኾነ!" በሚለው፡ በወንጌላዊው ጥቅስ መሠረት፡ "ፈጣሪ እግዚአብሔር፡ ሰው ኾነ!" የምንለው፡ 'ኢየሱስ ክርስቶስ' የተባለውን፡እግዚአብሔር ወልድን እንደመኾኑ መጠን፡ " ፍጡሩ ሰው፡ እግዚአብሔር ኾነ!" የምንለው ደግሞ፡ ድንግል ማርያምን መኾኑ ግልጽ ነው። (ዮሓ. ፩፥ ፲፬።)

በዚህ ረገድ፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዘወትሩ የጸሎታችን መግቢያ ላይ የምናውጀው ቃል አለ፤ ይኸውም፡ "ንሰግድ ለእግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፡ አሓተ ስግደተ፣ እንዘ አሓዱ ሠለስቱ፥ ወእንዘ ሠለስቱ አሓዱ፡ እንዘ ይሤለሱ በአካላት፤ ወይትዋሓዱ በመለኮት። ንሰግድ፡ ለእግዝእትነ ማርያም፡ ድንግል ወላዲተ አምላክ። ንሰግድ፡ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።"

ማለትም፡ "በአካላት፡ ሦስት፥ በመለኮትም፡ አንድ በመኾናቸው፡ አንድ ሲኾኑ፡ ሦስት፥ ሦስት ሲኾኑ፡ አንድ ለኾኑት፡ ለእግዚአብሔር አብና ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስም፡ አንዲት ስግደትን እንሰግዳለን። የአምላክ እናት ለኾነችው፡ ለእመቤታችን ድንግል ማርያም እንሰግዳለን። ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እንሰግዳለን።"

ደግሞም፡ "ስብሓት፡ ለእግዚአብሔር አብ፥ ስብሓት፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፥ ስብሓት፡ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ! ስብሓት፡ ለእግዝእትነ ማርያም፡ ድንግል ወላዲተ አምላክ! ስብሓት፡ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ!"

ማለትም፡ "ለእግዚአብሔር አብ፡ ምስጋና፥ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ምስጋና፥ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ምስጋና ይኹን! የአምላክ እናት ለኾነችው፡ ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ምስጋና ይኹን! ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል፡ ምስጋና ይኹን!" እያልን፡ ቀጥታ የአምልኮ ስግደትን እየሰገድን የምንጸልየውና የምናመሰግንበት፡ የምስጋና ጸሎት ነው።

ይህ የምስጋና ጸሎት የሚካኼደው፡ ሰው የኾነው፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከእርሷ፡ ከቅድስት እናቱ፡ ከድንግል ማርያምና ከመስቀሉ፡ ለአንዲት ቅጽበት እንኳ ሳይለይ፡ በተውሕዶ፡ ዐብሮ እንዳለ በማመን መኾኑ ሊታወቅ ይገባል። <u>በተዋሕዶ ምሥጢር፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ድንግል ማርያም ናት፤ ድንግል ማርያም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቅዱስ መስቀል፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅዱስ መስቀል ነው።</u> ፈጽመው አይለያዩምና።

እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ኹለቱን አካላትና ባሕርያት፡ ማለትም፡ <u>እግዚአብሔር ወልድንና ድንግል ማርያምን፥ እንዲሁም፡ በድንግል ማርያም ሰውነት የተገለጸውን እግዚአብሔር ወልድንና መስቀሉን፡</u> ፈጽመን አንለያያቸውም፤ የምናውቃቸውና የምናምንባቸው፥ የምናመልካቸውና የምንሰግድላቸው፡ በአንድነታቸው እንጂ፡ ተለያይተው በተናጠል አይደለም፤ በሥዕላችን እንኳ አንለያያቸውም፤ የተለያዩበት ሥዕል፡ ከኢትዮጵያዊነት ውጪ፡ ባዕድ ይኾናል።

እግዚአብሔር ወልድ ለኾነው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም እና ለቅዱስ መስቀሉ፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳችን ኾነን፡ የአምልኮ ስግደትን የምናቀርብላቸው፡ በዚህ ምክንያት ነው። ይህን እውነታ፡ ኹሉም ይወቀው! ለእነርሱ የምናቀርበው ስግደት፡ የአምልኮ እንጂ፡ የጸጋ፥ ወይም የአክብሮት አይደለም።

ስለዚህ፡ ለእግዚአብሔር አብ፡ የባሕርይ ልጁን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር የወለደችለት ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የአምላክ እናት በኾነች ጊዜ፡ ለእግዚአብሔር አብ፡ "ምኑ ኾነች!" ማለት ነው፤ "መርዓተ አብ!" ወይም፡ "የአብ ሙሽሪት!" ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክ፡ በአዳምና ሔዋን የንጽሓ ጠባይ ሕያው ሰውነት የመሠረተውን፡ ቅዱስ ጋብቻ፡ በዚህ ዕፁብ ድንቅ ሥራው፡ ለመደምደሚያው ፍጹምነት አብቅቶት፡ ዘለዓለማዊና እግዚአብሔራዊ ሥርዓት አድርጎታል።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪትና የእግዚአብሔር ወልድ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት የኾነችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዚህ ብቅዓቷ፡ የፈጣሪዋ፡ የክብሩ ብቻ ሳይኾን፡ በአምልኮቱም፡ በተዋሕዶ ምሥጢራዊ አንድነት፡ የእርሱ ተካፋይ ኾናለች።

እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለእርሷ፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ያለን፡ የእናትነት ፍቅር፡ በፍጹም አክብሮት ብቻ የተወሰነ ሳይኾን፡ የእርሷ ጥላና ምሳሌ ለነበረችው፡ ለታቦተ ጽዮን፡ ይቀርብላት ከነበረው አምልኮ ይልቅ በልጦ፡ ከመጨረሻውና መለኮታዊ ከኾነው፡ መንፈሳዊ ብቅዓት ደርሶ የሚፈጸም እንጂ፡ በምንም መልኩ የሚቀነስና የሚለወጥ አይደለም። በእርሷ አማካይነት፡ እግዚአብሔር በቸርነቱ ምልዓት፡ በመልኩ ለፈጠረውና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ላለው ሰብአዊ ፍጡሩ የለገሠውን፡ አምላካዊ ጸጋ፡ ማንም፡ ሊቀንሰው አይገባም።

ሰዎች፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚያወሷቸው ጥቅሶች ኹሉ፡ የእመቤታችንን፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ገናና ክብር ከፍ አድርገውና አጒልምሰው የሚያጸኑ እንጂ፡ በምንም መልካቸውና ይዘታቸው፡ የሚቀንሱባት አይደሉም፤ ምክንያቱም፡ ኹሉም፡ እርሷ፡ በሰውነቷና በሰብአዊት እናትነቷ፡ እግዚአብሔር ለኾነው ልጇ፡ ከማሕፀን ጀምራ፡ እስከዕርገቱ ድረስ፡ አንድም ቀን ሳትለየው፡ የእርሷ ድርሻዋ የኾነውን፡ ግዳጇን፡ በፍጹም ጥንቃቄና ትጋት ታካኼድና ትፈጽም እንደነበረ አረጋግጠው የሚያሳዩ ሲኾኑ፡ በልጇ፡ በኩል፡ የተነገረውና የተደረገው ኹሉ፡ አረጋግጦ የሚያሳየው ድርሻ ደግሞ፡ እርሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእግዚአብሔርነቱና በትስብእታዊ ተልእኮው ረገድ፡ ሊፈጽም የሚገባውን ግዳጅ ያከናወነ መኾኑን ነው።

አዎን! የእግዚአብሔር ወልድ እናት የኾነችው፡ ድንግል ማርያም፡ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ሕይወት በኾነው፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፥ እንዲሁም፡ የእርሱ አገልጋይና መልእክተኛ በኾነው በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤልና የመጥምቁ ዮሓንስ እናት በኾነችው፡ በቅድስት ኤልሣቤጥ አንደበት፡ እንደተመሰገነች፥ እርሷ ራሷም፡ እንደአክስቷ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልታ፡ "**ኵሉ ትውልድ፡ ያስተበፅዑኒ!**" ማለትም፡ "**ትውልድ ኹሉ ያመሰግኑኛል!**" እንዳለች፡ በብሥራቱ መጽሓፍ ውስጥ ተጽፎ የሚነበበው ቃል፡ ለምስክርነት ይበቃል። (ሉቃ. ፩።)

ይህ እውነታ፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት ውስጥ የኾነውን እንኳ፡ በምሳሌነት ብንወስድ፡ በዚያ ቤት ተፈጽሞ በታየው ተአምር፡ በገሃድ ተከሥቷል። አዎን! ያን የመሰለው፡ ተአምራዊ የድርጊት ውጤት የታየበትና የጋብቻ እግዚአብሔራዊ ሥርዓትነት የተረጋገጠበት፡ የቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት፡ ሰው የኾነችውን፡ የእናቱን ማንነትና ክብር፥ ሥልጣኗንና የበላይነቷንም ለመግለጥ፡ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእግዚአብሔርነቱ አረጋግጦ ሊመሰክርላት፡ በቀጥታ ያዘጋጀው መድረክ ኾኖ በመገኘቱ ነው።

ይኸውም፡ በሠርጉ በዓል ላይ እንዲገኙ ለተጋበዙትና ለታደሙት ኹሉ፡ "ይበቃል!" ተብሎ የተጠመቀው የድግሥ ጠጅ ማለቁን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአምላክነት ባሕርዩ እያወቀ ዝም ብሎ ሣለ፡ እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ "ወሶበ ኀልቀ ወይኖሙ፡ ትቤሎ እሙ፡ ለእግዚእ ኢየሱስ፡ 'ወይንኬ አልቦሙ!'" ማለትም፡ "ጠጁ ባለቀባቸው ጊዜ፡ እናቱ፡ ለጌታችን ኢየሱስ፡ 'ጠጅ እኮ አለቀባቸው!" ብላ፡ እስክትጠይቀው ድረስ፡ ለምን ጠበቀ? በእርግጥ፡ የእርሷ ማንነት፥ አሳቢነቷና ርኅራኄዋም እንዲገለጥ ስለፈለገ አይደለምን? አዎን! ነው።

ደግሞስ፡ "ምንት ብየ ምስሌኪ፡ ኦ ብእሲቶ! ዓዲ ኢበጽሐ ጊዜየ።" ማለትም፡ "እናቴ ሆይ! እኔ ካንቺ ጋር ምን አለኝ? ዳግመኛስ፡ ይህን የምትዪውን ለማድረግ እኮ ጊዜዬ አልደረሰም።" ብሎ ለመለሰላት ቃል፡ በእርሷ በኩል፡ ምንም ዓይነት መልስ ሳትሰጠው፡ በቀጥታ፡ አገልጋዮቹን ጠርታ፡ "ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ!" ማለትም፡ "ልጄ የሚላችሁን አድርጉ!" ብላ፡ ለእነርሱ ለሰጠችው ትእዛዝ፡ እርሱ፡ ልጇ፡ ምንም ሳያንገራግርና አንዳች መልስን እንኳ ሳያስሰማ፡ ትእዛዟን መፈጸሙ፡ በእናትና በልጅ፥ ደግሞም፡ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል፡ ያለው የፈቃድ ልዩነት፡ ወደፍጹም አንድነት ተመልሶ መጽናቱን አረጋግጦ አሳይቷል።

ሃይማኖታችንና አገራችን፥ እናታችንና ንግሥታችን የኾነችው፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ፈጣሪዋ ያቀዳጃትና እርሷም፡ ራስዋን ለፍጹምነት ያበቃችበት ማንነቷ፡ ማለትም፡ እውነተኛ መልኳና ባሕርይዋ፥ ስሟና ምግባርዋ፥ ክብሯና ማዕርጓ፡ በእኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ታማኞች ልጆቿ ዘንድ፡ ምንጊዜም አይለወጥም፤ በዚያው፡ ንጹሕና አማናዊ በኾነው ህላዌው፡ ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል እንጂ። ኢትዮጵያዊው ነቢይ ኤርምያስ፡ "ይዌልጥኑ ኢትዮጵያዊ፡ ማእሶ፥ ወነምርኒ፡ ኀበሪሁ!?" ማለትም፡ "በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን፥ ነብርም፡ ዝንጕርጕርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን!" ብሎ እንደተናገረው። የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪትና የእግዚአብሔር ወልድ እናት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም መቅደስ፡ የድንግል ማርያም ምንነትና ማንነት፡ ከቶ አይለወጥም!" (ኤር. ፲፫፥ ፳፫።)

## የቅዱሱን ኪዳን ተልእኮ በሚመለከት።

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የቅዱሱን ኪዳን ተልእኮ በሚመለከት፡ ቀድሞም ኾነ እስካኹን፥ ዛሬም፡ አጽንታ የቀጠለችው ሥርዓት፡ ያንኑ፡ ለ፯ሺ፭፻፮ (ለሰባት ሽህ አምስት መቶ ስድስት) ዓመታት፡ ሕያው ኾኖ የኖረውን፡ የፈጣሪዋን የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ሥርዓት እንጂ፡ ሰይጣናዊና ሟች የኾነውን፡ የሰዎችን ሥርዓት አይደለም። ያም፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት፡ በቅዱሱ ጋብቻ ላይ የተመሠረተው፡ ዘለዓለማዊ፥ ቤተሰባዊና ማኅበራዊ የኾነው፡ የህልውና ተልእኮ ነው።

የእግዚአብሔሩ የኾነው እርሱም፡ መጀመሪያ፡ በአዳምና በሔዋን፥ ተያይዞም፡ በእነኄኖክና ቅድስት ብእሲቱ፥ በነኖኅና ኀይከል፥ እስከመልከጼዴቅና ሳሌም፥ ከዚያም፡ ከኢትዮጵያዊው ኢያቄምና ከኢትዮጵያዊቷ ሓና ደርሶ፥ እግዚአብሔር አብ፡ በእርሱ ሙሽርነትና ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በወለደችለት በኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም ሙሽሪትነት፡ በዘለዓለማዊነት ያተመው፥ በመጨረሻም፡ በመለኮታዊ ትስብእትነቱ፡ ራሱ፡ በቃና ዘገሊላ ተግኝቶ የቀደሰውና ያጸደቀው ሥርዓተ ጋብቻ ነው።

እግዚአብሔር፡ ይህ ሥርዓቱ፡ በዚህ፡ በጋብቻ መልኩ ብቻ ሳይኾን፡ በሰብአዊው የጾታ ልዩነቱና የአካለ ሥጋ አባሎቹ፥ በተፈጥሮአዊው የዘር ፍትወቱና የልደት ውበቱ ጭምር፡ አሳምሮና አስጊጦ ባስገኘው፡ የሥነ ፍጥረት ትንግርቱ፡ አግዝፎና ሕያው አድርጎ፡ ለፍጹምነትና ለዘለዓለማዊነት አብቅቶታል።

ለዚህም ማረጋገጫ፡ ሌላ ምስክርና ማስረጃ አያስፈልግም። በቅዱሱ ኪዳን ውስጥ የተጠቃለሉት፡ ሰባቱም የእግዚአብሔር ቃል ኪዳናት፡ የተደረጉት፡ ኹሉም፡ በጋብቻ ሥርዓት ተውስነው በሚኖሩ ሕጋውያን ባልና ሚስት አማካይነት መኾኑ ብቻ ይበቃል፤ ይኸውም፡ ፩ኛ. አዳምና ሔዋን፤ ፪ኛ. ኖኅና ኀይከል፥ ፫ኛ፡ መልከ ጼዴቅና ሳሌም፥ ፬ኛ. አብርሃምና ሣራ፤ ፭ኛ. ሙሴና ሲጳራ፥ ፮ኛ፤ ዳዊትና ቤትሳባ፤ በመጨረሻም፡ እግዚአብሔር አብና ቅድስት ድንግል ማርያም መኾናቸው ነው።

ራሱ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለሓዋርያነት የጠራቸውና የመረጣቸው ደቀ መዛሙርቱ፥ በተለይም፡ ለሊቀ ሓዋርያነት የሠየመው ቅዱስ ጴጥሮስ ጭምር፡ ኹሉም፡ ቤተሰባዊ ሕይወትን፡ በሥርዓተ ጋብቻ መሥርተው፡ በትዳር ይኖሩና ለትዳር ኑሮ ይዘጋጁ የነበሩ ናቸው።

በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ የነበረው እጅግ ጥንታዊው የብሕትውናና የድንግልና አኗኗር ሥርዓት እንኳ ሳይቀር፡ ከግብፃውያኑ የምንኵስና ኑሮ፡ እጅግ የቀደመና የተለየ ሲኾን፥ ይኹን እንጂ፡ ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን መነኮሳት፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ፡ ከዘመናት በፊት መጥተው፡ ባስገኙላቸው ብሔራዊ ድክመት በመጠቀም፡ ያን እግዚአብሔራዊዉን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት አስወግደው፡ ይህን የራሳቸውን እስኪተኩ ድረስ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር በምትመራው፡ በሰፊዋ የኢትዮጵያ ዓለም ኹሉ ሠፍኖ ይሠራበት የነበረው፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓት እንደኾነ ግልጽ ነው።

ይህ፡ ጥንታዊዉ ኢትዮጵያዊ የእግዚአብሔር ሥርዓት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ **"አኮ፡ ለኵሉ ዘይትክሀል ዝንቱ፡ ዘእንበለ ለዘተውህቦ፤ እስመ ቦ ኅጽዋን፡ እለ ከማሁ ተወልዱ፡ እምከርሠ እሞሙ፤ ወቦ ኅጽዋን፡ እለ ኅጸውዎሙ ሰብእ፤ ወቦ ኅጽዋን፡ እለ ኅጸዉ ርእሶሙ፡ በእንተ መንግሥተ ሰማያት። ወዘሰ ይክል ተዐግሦ ለይትዐገሥ!"**

ማለትም፡ "ይህ፡ ለኹሉ የሚቻል አይደለም፤ ለተሰጠው ነው እንጂ። ከእናታቸው ማሕፀን፡ እንዲሁ የተወለዱ ዣንደረቦች አሉና፤ ሰዎች የሰለቧቸውም ዣንደረቦች አሉ፤ ስለመንግሥተ ሰማያት፡ ራሳቸውን ዣንደረባ ያደረጉ አሉ። መታገሥ የሚችልስ፡ ይታገሥ!" ብሎ፡ በአዲስ ኪዳኑ ዘመን የተናገረውን መለኮታዊ ቃሉን ተከትሎ ይፈጸም የነበረው ነው። (ማቴ. ፲፱፥ ፲፩-፲፪።)

ጌታችንም ይህን ቃል የተናገረው፡ ስለጋብቻና ስለትዳር ኑሮ፡ አይሁድ ፈሪሳውያን፡ በጠየቁት ጊዜ፡ ያለዝሙት ምክንያት፡ መፋታት እንደማይገባ ስለመለሰላቸው፡ "እመሰ ከመዝ ውእቱ፡ ሥርዓተ ብእሲ ወብእሲት፡ አኮ ሠናይ አውስቦ!" ማለትም፡ "የባልና የሚስት ሥርዓት፡ እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! ማግባት፡ መልካም አይደለማ!" ላሉት፡ ለደቀ መዛሙርቱ እንደነበረ ይታወሳል።

ይኹን እንጂ፡ በዚህ ረገድ፡ ጥንት፡ ከመጀመሪያው አንሥቶ፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ ሲሠራበት በኖረውና የእግዚአብሔር በኾነው፡ ኢትዮጵያዊው የጋብቻና የትዳር ሥርዓት ላይ፡ የኋላ ኋላ፡ እጅግ አስገራሚና አሳዛኝ የኾነ፡ የጥቃት ድርጊት ሊፈጸምበት በቃ፤ ይኸውም፡ የኢትዮጵያ የኾነው ይኸው የጋብቻ ሥርዓት፡ በራሱ፡ በቤቱና በአገሩ፥ በወገኑም ዘንድ ተንቆና ተዋርዶ፥ ተጥሎና ተወግዶ፡ በእርሱ ቦታ፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ ውርስና ቅርስ ላይ ተመሥርቶ፡ ይኸው ዛሬ፡ ሠልጥኖና ተንሠራፍቶ የሠፈነው፡ የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን፡ የምንኵስና ወግ፡ እንዲህ፡ መክበሩና ማስከበሩ፥ መግነኑና መንገሡ ነው።

ለዚህም ማረጋገጫው፡ ለጵጵስና የሚያበቃው፡ እርሱ ብቻ በመኾኑ፡ ዛሬ፡ ባላዋቂዎች ዘንድ፡ ከመመለክ ደረጃ የደረሰው፡ ይኸው ምንኵስና፡ "ጳጳስ" ተብሎ፡ ወደኢትዮጵያ የመጣው፡ የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን ተጠሪ፡ ወደኢትዮጵያ ተልኮ፡ በቅኝ ገዢነት ሥልጣኑ፡ መንበሩን፡ ከባለቤቱ ቀምቶ እስከያዘበት፥ ከዚያ ተያይዘው በቀጠሉትም ዘመናት፥ እስከቅርቡ ጊዜ ድረስ፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የመንፈሳዊው ዘርፍ የኾነው፡ የቤተ ክህነቱ ባለመንበር፡ እርሱም፡ የአኵሱሙ ንቡረ እድ፥ ኋላም፡ "ዕጨጌ" የሚል የማዕርግ ስም የተሰጠው፡ የኢትዮጵያው ሊቀ ካህናት፡ በቅዱሱ ጋብቻና በክቡሩ ትዳር ተወስኖ የሚኖር፡ ኢትዮጵያዊ ካህን መኾኑ፡ በገሃድ የታወቀበት እውነታ ነው። "አቦ ብልኀት! ዕጨግነት ከሚስት!" ይባል እንደነበረው።

እውነተኞቹን ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት፡ በተዋሕዶ አንድ አድርጋ፡ ዘለዓለማዊዉን መልካም ህልውናዋን በማካኼድ ላይ በምትገኘው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ይህ ፀረ እግዚአብሔርና ፀረ ኢትዮጵያ የኾነው፡ የባዕዳን አሠራር፡ አልኖረም፤ ዛሬም የለም፤ ወደፊትም፡ ሊኖር አይችልም። በአንድ ወገን፡ ሥርዓተ ጋብቻውና የትዳሩ ኑሮ፥ በሌላውም ወገን፡ የብሕትውናውና የድንግልናው አኗኗር፡ ኹለቱም ሥርዓቶች፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፡ እንደእግዚአብሔር ቃልና እንደመለኮታዊው መመሪያ፡ ተገቢ ሥፍራቸውንና ይዞታቸውን፥ ተፈጻሚነታቸውንና ፍሬያማነታቸውን እንደያዙ፡ እስከዛሬ ኖረዋል፤ ለወደፊቱም፡ በዘለዓለማዊነት ህልውናቸው ይቀጥላሉ።

ባሕታዊውና ድንግላዊው ቅዱስ ጳውሎስ እንኳ፡ አረማውያንና አሕዛብ ተከታዮቹ ለነበሩት፡ ለአዲሶቹ የክርስትና አማኞቹ በጻፋቸው መልእክቶቹ ውስጥ፡ በዚህ ረገድ: ለእነርሱ የሰጣቸው ቋሚ መመሪያ፡ ይህንኑ ጥንታዊዉንና አማናዊውን የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት መሠረት በማድረግና በማጽናት መኾኑን፡ ከዚህ የሚከተሉት፡ የአዲስ ኪዳኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች፡ አረጋግጠው ይመሰክራሉ።

ሀ . "እሙን ነገር፡ ዘይፈቅድ ይሠየም ጳጳሰ፡ ሠናየ ግብረ ፈተወ። ወባሕቱ ርቱዕ ይሠየም (ቀሲስ) ጳጳሰ፤ ዘኢያደሉ ለገጽ፥ ዘአልቦ ምክንያት፥ ዘአሐተ ብእሲተ አውሰበ፤ ብእሲ፡ ንቁህ ወጠቢብ፥ ወመፍቀሬ ነግድ፥ ዘአንጽሐ ርእሶ፥ መምህር ወመገሥጽ፤ ዘኢያበዝኅ ሰትየ ወይን፥ ዘኢያፈጥን እዴሁ ለዘቢጥ፥ ባቍዕ፥ ዘኢይትገአዝ፤ ዘኢያፈቅር ንዋየ፤ ዘሠናይ ሥርዓተ ቤቱ፥ ዘቦ ውሉድ፡ ዘይትኤዘዙ በኵሉ ንጽሕ፤ ወዘሰ ኢይክል፡ ሠሪዐ ቤቱ፡ እፎኑ ያስተሓምም ቤተ እግዚአብሔር።"

ማለትም፡ "ጵጵስናን ሊሾም የሚወድድ ቢኖር፡ መልካም ሥራን ተመኘ!' የሚለው ቃል፡ የታመነ ነገር ነው። ነገር ግን፡ ጳጳስ ኾኖ ሊሾም የሚገባው፡ ፊት አይቶ የማያደላ፥ ምክንያት የሌለበት፥ የአንዲት ሚስት ባል፥ ንቁ ሰው፥ ብልህ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ራሱን፡ በንጽሕና የጠበቀ፥ የሚመክር፥ የሚያስተምር፥ የማይሰክር፥ ለመማታት የማይፋጠን፥ በምክሩ የሚጠቅም፥ የማይጣላ፥ ገንዘብ የማይወድድ፥ ቤተሰቡን፡ በመልካም የሚያስተዳድር፥ በፍጹም ንጽሕና የሚታዘዙ ልጆች ያሉት፤ ቤቱን በሥርዓት መያዝና መምራት የማይችል ሰው፡ የእግዚአብሔርን ቤት፡ እንደምን ያስተዳድራል?" (፩ጢሞ. ፫፥ ፩-፫።)

በ . "ብእሴ፡ ዘአሐተ ብእሲተ አውሰበ፥ ኅሩየ፥ ዘኢየሓምይዎ በእኩይ፥ ዘቦ ውሉድ ማሃይምናን፡ ዘኢያስተዋድይዎሙ በምርዓት፡ እለ ኢኮኑ ዝሉፋነ እለ ይቴዘዙ፡ ወርቱዕ ይሠየም ጳጳስ።"

ማለትም፡ "ጳጳስ ኾኖ ሊሾም የሚገባው፡ የአንዲት ሚስት ባል የኾነ፥ የተመረጠ፥ በክፉ ነገር የማያሙት፥ በዝሙት ያልተከሰሱና ያልተነቀፉ፥ የሚታዘዙና የታመኑ ልጆች ያሉት ይኹን!" (ቲቶ ፩፡ ፮-፯።)

\+ \+ \+

ተዐውደ፡ በታኅሣሥ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፮ ዓመተ ምሕረት፡ ታወጀ።

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፤
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፤
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።